ቁጥር/Ref.No ገንዘብ/ኮሚ/126
ቀን/Date 23/11/2018

ለአማራ ክልል ገቢዎች ቢሮ

ባህርዳር

ጉዳዩ፡- <u>የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ፣</u>

በክልሉ የገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 301/2018 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋዮች በቁርጥ ለሚወሰንላቸው ተሸከርካሪዎች ከመቀጠር የሚገኝ ግብር ማስከፈያ መመሪያ በፍትህ ቢሮ አስተያየት የተሰጠበት እና በቢሮው የፀደቀውን የአፈጻጸም መመሪያ ስራ ላይ እንዲውል በየደረጃው ለሚገኙ ተቋማት በማሳወቅ ለአፈፃፀሙ ተገቢውን ክትትል እንድታደርጉ በማለት አሳውቃለሁ።

"ከሰላምታ ጋር"

አታላይ ጥላሁን ጫኔ
ቢሮ ኃላፊ

ግልባጭ//

- ለ ----------ዞንና ከተማ አስተዳደር ገንዘብ መምሪያ
- ለቢሮው ህግ አገልግሎት ክፍል
- ለፊስካል ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት

<u>ገንዘብ ቢሮ</u>

መመሪያ ቁጥር 148/2018 ዓ/ም

በአማራ ብሔራዊ ክልል ውስጥ ለሚገኙ በተለያየ የንግድ ሥራ እና ቤት በማከራየት ለተሰማሩ የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋዮች እና በቁርጥ ለሚወሰንላቸው ተሽከርካሪዎች ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር አወሳሰን መመሪያ

ሀገራዊ እና ክልላዊ የኢኮኖሚ እድገት እንዲሁም የምንከተለው የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ስርዓት አንፃር የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ለማበረታታት እና የተጀመረውን ሀገራዊ የታክስ ሪፎርም የበለጠ በማጠናከር ጤናማ የገበያ ውድድር እንዲፈጠር ለማድረግ፤

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 (በአዋጅ ቁጥር 276/2013 እንደተሻሻለ) እንዲሁም የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 83/1995 ዓ.ም (በአዋጅ ቁጥር 196/2003፣ 2012/2006 እና 270/2013 እንደተሻሻለ) ተሸረዉ ከላይ በተገለጸዉ የገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 301/2018 ዓ.ም የተተኩ መሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 100 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገ ሲሆን ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፤

በአዲሱ የገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 301/2018 ዓ.ም መሰረት የገቢ ግብር የማስከፈያ ምጣኔ ተሻሽሎ የተቀመጠ ስለሆነ ከዚህ የተሻሻለ ምጣኔ ጋር አብሮ የሚሄድ መመሪያ አሻሽሎ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የወቅቱን የገበያ ዋጋ እና የንግድ እንቅስቃሴን በትክክል በሚያሳይ መንገድ የግብር ከፋዮችን የቀን ገቢ ጥናት እንደገና በማጥናት መወሰን የክልሉን ገቢ የመሰብሰብ አቅም ለማሳደግ እና የግብር ከፋዮችን የደረጃ ምደባ ማካሄድ በማስፈለጉ፤

በክልሉ ውስጥ በንግድ ሥራ እና ቤት በማከራየት ሥራ ዘርፍ የተሠማሩ እና ወደ ግብር መረቡ ያልተካተቱ ግብር ከፋዮችን ለይቶ ሙሉ በሙሉ ወደ ግብር መረቡ በማካተት ፍትሃዊነትን በማረጋገጥ የሚፈለግባቸውን ግብር እና ታክስ በወቅቱ ወስኖ እንዲከፍሉ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብ ቢሮ በገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 301/2018 አንቀጽ 98 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "በአማራ ብሔራዊ ክልል ውስጥ ለሚገኙ በተለያየ የንግድ ሥራ እና ቤት በማከራየት ለተሰማሩ የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋዮች እና በቁርጥ ለሚወሰንላቸው ተሸከርካሪች ከመቀፀር የሚገኝ ገቢ የግብር አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 148/2018 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጉም**

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1/ "ቤት ማከራየት" ማለት ለመኖሪያ ወይም ለንግድ ስራ አገልግሎት ማንኛውንም ቤት በማከራየት ጥቅም ማግኘት ሲሆን ህንፃን በማከራየት የሚገኝ ጥቅምንም ይጨምራል፤

2/ "የግምት ታክስ ስሌት" ማለት ማንኛውም ታክስ ከፋይ በታክስ ሕግ መሠረት ማቅረብ የሚገባውን የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ እንደሆነ ወይም በግምት ከመወሰኑ በፊት ካላቀረበ ወይም የሒሳብ መዝገብ ሳያቀርብ ገቢውን ያስታወቀ ወይም ሂሳብ መዝገቡ ተቀባይነት ባያገኝ ወይም ቢሮው በራሱ

በማጽናት ወይም በመቀነስ ወይም በመጨመር የሒሳብ መዝገቡን ያሻሻለ እንደሆነ በማንኛውም ጊዜ የሚያገኘውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ ግብር ከፋዩ ሊከፍለው የሚገባውን የግብር መጠን የሚገልጽ ስሌት ነው፤

3/ "መደበኛ የግምት አወሳሰን" ማለት በሒሳብ መዝገብ ወይም ግልጽ የግዥና ሽያጭ መረጃ ወይም ስለንግድ እንቅስቃሴያቸው ከሦስተኛ ወገን መረጃ ለማግኘት በማይቻልበት ጊዜ ዝቅተኛውን ዓመታዊ ሽያጫቸውን በመውሰድ አስቀድሞ የተወሰነን የሥራ ዘርፍ ግብር ለመወሰን የሚያሰችል ስልት ነው፤

4/ "ያልተጣራ ትርፍ" ማለት ገቢያቸውን በሂሳብ መዝገብ እንዲያሳውቁ ለሚገደዱ የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ወይም በፈቃደኝነት የሂሳብ መዝገብ ለሚያቀርቡ የደረጃ "ለ" ከሽያጭ ገቢ ላይ የግዢ ወጪ ብቻ በመቀነስ የሚገኝ ትርፍ ነው፤

5/ "የኮሚሽን ገቢ" ማለት በሕግ ወይም ውልን ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል በጸደቀ ውል በተወሰነው መሰረት ከአንድ እቃ ወይም አገልግሎት ዋጋ ላይ ለእቃ አቅራቢው ለአገልግሎት ሰጪው የሚከፈል ገንዘብ ነው፤

6/ "የወኪል ንግድ" ማለት የአንድ አምራች ወይም አስመጪ ምርትን ወይም አገልግሎትን በራሱ በመግዛት የምርቱን ወይም የአገልግሎቱን የመሸጫ ዋጋ በወካዩ እየተወሰነ የሚሰራ ሥራ ነው፤

7/ "የሦስተኛ ወገን መረጃ" ማለት የታክስ ከፋዩን የታክስ ግዴታ በአማራጭ መንገድ ለመወሰን የሚያገለግል የግዥ ወይም የሽያጭ ሠነድ ከሶስተኛ ወገን የሚገኝ መረጃ ነው፤

8/ "አዋጅ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 301/2018 ዓ.ም ነዉ፤

9/ "የታክስ አስተዳደር አዋጅ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ዓ.ም ነው፤

10/ "ደንብ" ማለት የገቢ ግብር አዋጅ እና የታክስ አስተዳደር አዋጅን ለማስፈጸም በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የወጣን ደንብ ይመለከታል፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ገንዘብ ቢሮ

11/ “ቢሮ” ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገንዘብ ቢሮ ነው፤

12/ “ገቢዎች ቢሮ” ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ ነዉ፡፡

13/ “ጽህፈት ቤት” ማለት በየደረጃው የሚገኝ የገቢዎች ቢሮ ተዋረድ መስሪያ ቤት ሲሆን የወረዳ ጽ/ቤቶችን እና ክፍለ ከተሞችን ይጨምራል፤

14/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

15/ በወንድ ፆታ የተገለፀ ማንኛውም ድንጋጌ የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

3. **የመመሪያው ተፈጻሚነት**

ይህ መመሪያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 301/2018 አንቀጽ 3 መሰረት ደረጃ "ሀ" እና “ለ” ተብለው በክልሉ ውስጥ የተመደቡ ግብር ከፋዮች እና በአዲስ ወደ ግብር መረቡ የተካተቱ በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ግለሰብ ነጋዴዎች ወይም በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ ቤት የሚያከራዩ ግለሰቦች ወይም የሕግ ሰውነት የተሰጣቸው ድርጅቶች እንዲሁም በተሽከርካሪ ስራ በመቀጠር የሚሰሩትን የሥራ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ በሚገደዱ ግለሰብ ወይም ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች የግብር አወሳሰን

4. **በተሽከርካሪ ስራ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢን በግምት ግብር ስለመወሰን**

1/ ለሁሉም የተሽከርካሪ ዓይነት ዝቅተኛ የሾፌርና የረዳት ደመወዝ በቁርጥ የሚወሰን ሲሆን የተሳቢ ተሽከርካሪ ተጎታችና ጎታች እንደ አንድ ተሽከርካሪ የሚቆጠሩ ስለሆነ በመጫን አቅሙ የተመለከተው የሾፌርና የረዳት ደመወዝ ተወስዶ የመቀጠር ገቢ ይወሰናል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የኮንስትራክሽን ተሽከርካሪ አከራይ ሹፌርና ረዳት ግብር በመደበኛ የግብር አከፋፈል ሥርዓት ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ በቀረበው ሠንጠረዥ ወይም በሶስተኛ ወገን ግብይት መረጃ ላይ በመመስረት የሚወሰን ይሆናል።

3/ የኮንስትራክሽን ተሽከርካሪዎች የሾፌርና ረዳት የሥራ ግብር ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ የቀረበውን ሠንጠረዥ ከሚቀርበው ወርሃዊ የሥራ ግብር ወይም ከሶስተኛ ወገን መረጃ ጋር በማነጻጸር በተሻለው የሚወሰን ወይም የሚከፈል ይሆናል።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኮንስትራክሽን ተሽከርካሪዎች የሾፌርና ረዳት የስራ ግብር በየወሩ ከተቀጣሪው ተቆርጦ ለገቢ ተቋሙ የሚከፈል ይሆናል።

5. ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ በግምት ግብር ስለመወሰን

1/ በግለሰብ ግብር ከፋዮች የኪራይ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑት የኪራይ ገቢ ምጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው።

ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ በዓመት		የኪራይ ገቢ ግብር መጣኔ
ከብር	አስከ ብር	
0	24,000	0%
24,001	48,000	15%
48,001	84,000	20%
84,001	120,000	25%
120,001	168,000	30%
ከ168,000	በላይ	35%

2/ በአከራይና በተከራይ መካከል የተፈጸመ የኪራይ ውል ስምምነት የገንዘብ መጠን ትክክለኛነቱ በገቢ ተቋሙ ተቀባይነት ካገኘ በውል ስምምነቱ መሠረት ግብር ይወሰናል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ግብር ከፋዩ ያቀረበው ማስረጃ ተዓማኒነት ከሌለው እና ከሦስተኛ ወገን መረጃ ከተገኘ ተነጻጽሮ የተሻለው ተወስዶ ግብር ሊወሰን ይችላል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት መወሰን ካልተቻለ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 3 መሠረት ወቅታዊ ትክክለኛ የኪራይ ዋጋ ጥናት ተወስዶ የግብር ስሌቱ የሚሰራ ይሆናል፡፡

5/ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የሌለበት የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ ግብር በሚሰላበት ጊዜ ከግብር ዓመቱ ጠቅላላ የኪራይ ገቢው ውስጥ ለቤቶቹ፣ ለቤት ዕቃና መሣሪያ ማደሻ፣ መጠገኛና ለእርጅና መተኪያ የሚሆን ከኪራዩ ጠቅላላ ገንዘብ ላይ እንደ ወጪ 50% ተይዞ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ግብሩ የሚወሰን ይሆናል፡፡

6/ ሂሳብ መዝገብ የማቅረብ ግዴታ የሌለበት የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ ወይም አከራይ ከአንድ ዓመት በላይ የሚሸፍን የኪራይ ክፍያ የተቀበለ እንደሆነ የኪራይ ገቢው በግብር ዘመኑ ተጠቃሎ ተይዞለት ግብሩ ገቢው ለሚሸፍናቸው ዓመታት ተሸንሽኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 በተመለከተው ምጣኔ መሰረት እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 በተመለከተው መንገድ ከአንድ ዓመት በላይ የሚቆይ የኪራይ ውል የውል ዘመኑ ከማለቁ በፊት የተቋረጠ እንደሆነና ለተከራይ ቀሪ ክፍያ መመለሱ በማስረጃ ሲረጋገጥ በብልጫ የከፈለው ተሰልቶ ሊመለስለት ወይም ለቀጣይ የግብር ዘመን ታክስ ከፋዩ በጽሁፍ ፍላጎቱን ሲገልጽ በታሳቢነት እንዲያዝለት ይደረጋል፡፡

6. የንግድ ሥራ ገቢ ግብር በግምት ስለመወሰንና ስለመሰብሰብ

1/ ለደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች ግብር የሚወሰነው ከዚህ በታች በተቀመጠው የግብር ማስከፈያ ሠንጠረዥ መሠረት ይሆናል፡፡

ግብር የሚከፈልበት አመታዊ ጠቅላላ ገቢ		መጣኔ
ከብር	አስከ ብር	
0	100,000	2%
100,001	500,000	3%
500,001	1,000,000	5%
1,000,001	1,500,000	7%
1,500,001	2,000,000 በታች	9%

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ለሚከተሉት ተፈጻሚ አይሆንም፦

ሀ) የሚከተሉትን ጨምሮ የሙያ አገልግሎት ለሚሰጡ ሰዎች፦

i. ለሂሳብ አያያዝ ሙያ፣
ii. ለኦዲት ባለሙያ፣
iii. ለአርኪቴክቸር፣
iv. የኢንጂነሪንግ፣
v. የቅየሳ፣
vi. ለአማካሪዎች፣
vii. ለግንባታ ስራ ተቋራጮች፣
viii. ለመሃንዲሶች፣
ix. ለፋይናንስ፣ ለኦኮኖሚ እና ለኢንቨስትመንት ባለሙያዎች፣
x. ለጤና ባለሙያዎች፣
xi. ለሕግ ባለሙያዎች፣
xii. የአስተዳደር፣
xiii. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ፣

xiv. ማህበራዊ ጉዳይ፣ ወይም

xv. በሌላ ተመሳሳይ መስክ የሚሰጥ የሙያ አገልግሎት፣

ለ) ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች እና

ሐ) የሂሳብ መዝገብ በማቅረብ በሠንጠረዥ "ሐ" መሰረት በተጣራ ታክስ የሚከፈልበት ገቢ ላይ ግብር ለመክፈል ለመረጡ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አዲስ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች በቀን ገቢ ጥናት አመታዊ ገቢያቸው ከብር 2,00,000.00 (ሁለት ሚሊዮን) እና በላይ የሆኑ ግብር ከፋዮች ግብራቸው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተቀመጠው ከፍተኛ ምጣኔ 9% የሚወሰን ይሆናል።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የግብር ውሳኔ የተሰጣቸው ግብር ከፋዮች ለቀጣይ የግብር ዘመን ለግብር ከፋዩ የደረጃ ሽግግር ማድረጉን እና ሂሣብ መዝገብ እንዲይዙ በደብዳቤ ሊገለጽላቸው ይገባል።

5/ የቀን ገቢያቸው ያልተጠኑ አዲስ ግብር ከፋዮች በገቢ ጽህፈት ቤት የቀን ገቢ ግምት አጥኝ ኮሚቴዎች/ሙያተኞች/ እየተጠና በግብር አወሳሰን፣ አስተዳደርና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት ወይም የገቢ አሰባሰብ ክትትል ቡድን አማካኝነት እየፀደቀ ሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ የማይገደዱ ግብር ከፋዮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ግብሩ ይወሰናል፤

6/ በዚህ መመሪያ መሰረት የቀን ገቢ ጥናት የተጠኑ ግብር ከፋዮች የተለዩ እንቅስቃሴ ወይም ተጨማሪ የንግድ ስራ ዘርፍ ወይም ከሶስተኛ ወገን የግብይት መረጃ ካልተገኘ ወይም ካልቀረበ እንደገና ማጥናት ሳያስፈልግ በተጠናዉ የቀን ገቢ ግምት መረጃ መሰረት እንዲከፍሉ ይደረጋል።

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተጠናውን የቀን ገቢ ግምት ጥናት ግብር ከፋዩ ቅሬታ አቅርቦ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴም በመቀነስ ወይም በመጨመር ከተሻሻለ በቀጣይ ግብር ዘመን የቀን ገቢ ግምት ተጠንቶ በሚቀርበው መረጃ መሰረት ግብሩ ይወሰናል፡፡

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በተጠና የቀን ገቢ ጥናት ላይ ይግባኝ በመጠየቅ በመቀነስ ወይም በመጨመር የተሻሻለባቸውና የተወሰነባቸው ግብር ከፋዮች በቀጣይ ዓመት የቀን ገቢ ግምት የሚጠና ይሆናል፡፡

9/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 እና 8 መሠረት የቀን ገቢ ጥናት ሲጠና የወቅቱን የንግድ እንቅስቃሴ ግምት ውስጥ በማስገባት አጥንቶና ግብር ወስኖ የመስጠት ኃላፊነት የገቢ ተቋሙ ተግባር ይሆናል፡፡

7. በሶስተኛ ወገን የግብይት መረጃ ግብር ስለመወሰንና ስለመሰብሰብ

1/ ከሦስተኛ ወገን በሚሰበሰብ የግብይት መረጃ ላይ ተመስርቶ ግብር የሚወሰንባቸው የንግድ ዘርፎች ላይ የተሰማራ ነጋዴ ትክክለኛ እና ተዓማኒነት ያለው መረጃ ከተገኘ የግብይት መረጃው እና የቀን ገቢ ግምቱ ተነጻጽሮ የተሻለው ተወስዶ ግብሩ የሚወሰን ይሆናል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተደነገገው የደረጃ “ለ” ግብር ከፋይ ሆኖ ከሶስተኛ ወገን በተገኘ የግዥና የሽያጭ መረጃ ብቻ ተመስርቶ ግብራቸው ለሚወሰንላቸው ግብር ከፋች የግዥን መረጃ ወደ ሽያጭ በመቀየር ሽያጩ ከብር 2,000,000.00 (ሁለት ሚሊዮን) በታች ከሆነ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ሠንጠረዥ መሠረት ግብር ይወሰናል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቆ ሆኖ አዲስ የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች ከሶስተኛ ወገን በተገኘ የግዥና የሽያጭ መረጃ ላይ ብቻ ተመስርቶ ግብራቸው ለሚወሰንላቸው ግብር ከፋዮች የግዥን መረጃ ወደ ሽያጭ በመቀየር ሽያጩ ከብር 2,00,000.00 (ሁለት ሚሊዮን)

እና በላይ የሆኑ ግብር ከፋዮች ግብራቸው በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተቀመጠው ከፍተኛ ምጣኔ 9% የሚወሰን ይሆናል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከሶስተኛ ወገን በተገኘ የግዥና የሽያጭ መረጃ ላይ ተመስርቶ ግብር የሚወሰንላቸው ግብር ከፋዮች የአካባቢ መሸጫ ዋጋ ከተገኘ የሦስተኛ ወገን የግዥ መረጃውን በአካባቢ መሸጫ ዋጋ በማባዛት ወደ ሽያጭ በመለወጥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ሠንጠረዥ መሠረት ግብሩ ይወሰናል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሦስተኛ ወገን የተገኘ የግብይት መረጃው ወይም የግዥ መረጃ የአካባቢ የመሸጫ ዋጋ ካልተገኘ ወደ ሽያጭ የሚቀየረው በሚከተለው ቀመር ይሆናል፡፡

$$\text{ሽያጭ} = \left\{ \frac{\text{ግዥ}}{100 - \text{ያልተጣራ የትርፍ ምጣኔ}} \right. \times 100\%$$

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ዓመታዊ ሽያጫቸው ከብር 2,000,000.00 (ሁለት ሚሊዮን) እና በላይ የሆነ ግብር ከፋይ ከሚቀጥለው በጀት ዓመት ጀምሮ የደረጃ ሽግግር ስለማድረጉ፤ ደረጃውንና ግዴታውን አዉቆ በገቢ ግብርና ታክስ አሰተዳደር አዋጅ የተጣሉ ግዴታዎችን በወቅቱ እንዲወጣ በደብዳቤ መገለጽ አለበት፡፡

8. በጣምራ ግብር ስለመወሰንና ስለመሰብሰብ

1/ በክልሉ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች በግብር ከፋዩ ስም የተጠና የቀን ገቢ ግምት ከቀረበ ወይም ከተገኘ በየንግድ ዘርፉ ሊጣመር የሚችል መሆኑ እየተረጋገጠ በማጣመር ወይም በመደመር ዓመታዊ ገቢው ከብር

2,000,000.00 (ሁለት ሚሊዮን) በታች ከሆነ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ሠንጠረዡ መሠረት በመጠቀም ግብሩ ይወሰናል፡፡

2/ በዚህ እንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው ቢኖርም በክልሉ ውስጥ አመታዊ ገቢያቸው 2,000,000.00 (ሁለት ሚሊዮን) በላይ ሆኖ በጣምራ ግብር ለሚወሰንላቸው ግብር ከፋዮች በተለያዩ የንግድ ዘርፎች የተገኘውን ገቢ በመደመር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተቀጠውን ከፍተኛ ምጣኔ 9% እየተሰላ ግብር ይወሰናል፡፡

3/ በዚህ መመሪያ መሠረት የቀን ገቢ ጥናት ያልተጠናላቸው ግብር ከፋዮች በገቢ ጽ/ቤት የቀን ገቢ ግምት አጥኝ ኮሚቴዎች/ሙያተኞች/ እየተጠና በግብር አወ/አሰ/ክትትል ዋና የሥራ ሂደት ወይም የገቢ አሰባሰብ ክትትል ቡድን አማካኝነት እየፀደቀ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2 እና 3 መሠረት ግብሩ ይወሰናል፤

9. መደበኛ የግምት አወሳሰን

የሚከተሉት የንግድ አገልግሎቶች ከዚህ በታች በተገለጹት በመደበኛ የግምት አወሳሰን መሠረት ግብሩ የሚወሰን ይሆናል፡፡

1/ የወፍጮ ቤት አገልግሎት ንግድ

ሀ) ወፍጮ ከሥራ ባህሪያቸው አንጻር በቁርጥ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ማስከፈያ ሠንጠረዥ ላይ የተቀመጠውን ሽያጭ በመውሰድ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 በተቀመጠው ሠንጠረዥ መሰረት ተሰልቶ ግብር የሚወሰን ይሆናል፡፡

ለ) ከአንድ በላይ ቋት ያለው ግብር ከፋይ ጠቅላላ ሽያጩን ገቢ ለማስላት ለእያንዳንዱ ቋት በማስከፈያ ሠንጠረዡ ላይ የተመለከተውን የገቢ መጠን በቋቱ በማባዛት ጠቅላላ ገቢውን መሠረት ተደርጎ በዚህ መመሪያ አንቀጽ

6 ንዑስ አንቀጽ 1 በተቀመጠው ሠንጠረዥ መሰረት ተሰልቶ ግብር የሚወሰን ይሆናል፡፡

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ" የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቋት ብዛት የሚወሰነው እያንዳንዱ ዲናሞ የሚያንቀሳቅሰውን የቋት ብዛት በባለሙያዎች በክትትል ተረጋግጦ ለጽህፈት ቤት ኃላፊ ሲቀርብና ሲጸድቅ ብቻ ነው፡፡

2/ የተሸከርካሪ ትራንስፖርት አገልግሎት ንግድ

ሀ) ተሸከርካሪ ከሥራ ባህሪያቸው አንጻር በቁርጥ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ማስከፈያ ሠንጠረዥ ላይ የተቀመጠውን ሽያጭ በመውሰድ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 በተቀመጠው ሠንጠረዥ መሰረት ተሰልቶ ግብር የሚወሰን ይሆናል፡፡

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" የተደነገገው ቢኖርም ተሸከርካሪው ከመደበኛ ስምሪት ውጭ ከተከራየ በሶስተኛ ወገን መረጃ ወይም በቀን ገቢ ጥናት መሰረት ዓመታዊ ሽያጩ ከብር 2,000,000.00 (ሁለት ሚሊዮን) በታች ከሆነ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 በተቀመጠው ሠንጠረዥ መሰረት ተሰልቶ ግብር የሚወሰን ይሆናል፡፡

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ለ" የተደነገገው ቢኖርም ተሸከርካሪው ከመደበኛ ስምሪት ውጭ ከተከራየ በሶስተኛ ወገን መረጃ ወይም በቀን ገቢ ጥናት መሰረት ዓመታዊ ሽያጩ 2,000,000.00 (ሁለት ሚሊዮን) በላይ ከሆነ በመደመር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተቀመጠውን ከፍተኛ ምጣኔ 9% እየተሰላ ግብር ይወሰናል፡፡

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ለ" እና "ሐ" የተደነገገው ቢኖርም ተሸከርካሪ ከመደበኛው ስምሪት ውጭ ከተከራየ ከሶስተኛ ወገን መረጃ

ወይም በቀን ገቢ ጥናት መሰረት ዓመታዊ ሽያጫቸው በቁርጥ ከተቀመጠው የሽያጭ መጠን በታች ሊሆን አይችልም።

ሠ) የትራንስፖርት ንግድ ሥራ ግብር የሚወሰነው ተሸከርካሪው የተመረተበትን ዘመን መሠረት ተደርጎ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሠረት ይሆናል።

i. የህዝብ ማመላለሻ የሆኑ ትራንስፖርት ዓይነቶች በመቀመጫ ወንበር ብዛት፤
ii. የደረቅ ጭነት ትራንስፖርት ዓይነቶች በጭነታቸው መጠን (በኩንታል)፤
iii. የፈሳሽ ጭነት ትራንስፖርት ዓይነቶች በሚይዙት የፈሳሽ መጠን (በሊትር)፤
iv. የተሳቢ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም የሚወሰነው የጎታችና የተጎታች የመጫን አቅም ተደምሮ እንደ አንድ ተሽከርካሪ የሚቆጠር ሲሆን የተመረተበት ዘመን የተለያየ ከሆነ የጎታቹ የሥሪት ዘመን ተወስዶ የሚወሰን ይሆናል።
v. ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ለብቻው ሲሆን የመጫን አቅሙ በሊብሬው ላይ በተገለጸው መሠረት ሲሆን በሊብሬው ላይ የመጫን አቅሙ ያልተገለጸ እንደሆነ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ረ" ከዚህ በታች የተመለከተውን ቀመር መሠረት በማድረግ የተሽከርካሪ የአክስል ክብደት የመጫን አቅሙ ተደርጎ ተወስዶ፤
vi. ተጎታቹ የተሸከርካሪ አካል ለብቻው ሲሆን በሊብሬ ላይ የተገለጸው የመጫን አቅም ተወስዶ፤ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 በተቀመጠው ሠንጠረዥ መሰረት ተሰልቶ ግብር የሚወሰን ይሆናል።

ረ) ለዚህ ንኡስ አንቀጽ ፊደል ተራ “ሠ” የንዑስ ንዑስ ቁጥር “V” አፈጻጸም፡

$$\text{የመጫን አቅም} = \frac{\text{የአክስል ክብደት (ጠቅላላ ክብደት - ነጠላ ክብደት)}}{100}$$

“አክስል” ማለት የተሽከሪካሪ ጎማ ታስሮበት የሚዛውር የብረት ዘንግ ነው፡፡

“የአክስል ክብደት” ማለት በተሽከርካሪ ሊብሬ ላይ የተገለጸውን መረጃ መሠረት በማድረግ

ከተሽከርካሪው ጠቅላላ ክብደት ላይ ነጠላ ክብደትን በመቀነስ የሚገኝ ውጤት ነው፡፡

“የመጫን አቅም” ማለት በኪሎ ግራም የሚገለጸውን የተሽከርካሪ የአክስል ክብደትን ለ100 በማካፈል በኩንታል የሚገለጽ ውጤት ነው፡፡

ሰ) በክልሉ ውስጥ ዓይነታቸውና የምርት ዘመናቸው የተለያዩ ተሽከርካሪዎች ያሉት ታክስ ከፋይ በየተሽከርካሪው የተገኘ ገቢ ተደምሮ የሚገኘው ጠቅላላ ገቢ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 በተቀመጠው ሠንጠረዥ መሰረት ተሰልቶ ግብር የሚወሰን ይሆናል፡፡

ሸ) የተሽከርካሪው የግብር ዓመቱ ከፊል ጊዜ ብቻ ስራ ላይ መዋሉ ከተረጋገጠ ከዓመት ገቢው በወራቱ ተሰልቶ ግብር እንዲከፍል ይደረጋል፡ ፡

ቀ) የተሽከርካሪ ባለንብረት ራሱ የሚያሽከረክር ከሆነ ለሾፌር ይከፈል የነበረውን የደመወዝ ዓመታዊ ግብር ከተሽከርካሪ ዓመታዊ ግብር ጋር ተደምሮ ግብር ይከፍላል፡፡

በ) የተሽከርካሪ ዓመታዊ ግብር በሚከፈልበት ጊዜ የረዳትና የሾፌር ከመቀጠር የሚገኘው ገቢ በአንድነት የሚከፈል ይሆናል፡፡

ተ) ለዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈጻጸም የተሽከርካሪ የትራንስፖርት አገልግሎት የጋሪ እና የሞተር ሳይክል ተሽከርካሪ አገልግሎትን ይጨምራል፡፡

3/ የእርሻ አገልግሎት ተሽከርካሪ ንግድ

ሀ) ለእርሻ አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ንግድ ሥራ ግብር የሚወሰነው ተሽከርካሪው የተመረተበት ዘመን መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ዓይነት ዓመታዊ ገቢ እና የግብር መጠን ስሌት ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው በቁርጥ ግብር ሠንጠረዥ መሠረት ይሆናል፣

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ "ሰ"፣ "ሸ"፣ "ቀ" እና "በ" ላይ የተመለከቱት ለዚህ ንዑስ አንቀጽም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

4/ የኮንስትራክሽን መሣሪያ ኪራይ

ሀ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት ታክሳቸው በግምት የሚወሰነው የኮንስትራክሽን መሣሪያ ባለቤትነት (ሊብሬ) በከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር አማካይነት የተሰጠው እና ለኮንስትራክሽን ሥራ የሚከራይ ተብሎ የተገለጸ መሳሪያ ነው፡፡

ለ) የኮንሰትራክሽን ተሽከርካሪ አከራይ ግብሩ በግምት የሚወሰነው ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገውና ለኮንስትራክሽን መሳሪያ ኪራይ እንዲያገለግል እንደ የተሽከርካሪው የመጫን አቅም የተመለከተውን በመደበኛ የግምት ግብር አወሳሰን ሥርዓትን መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

ሐ) የኮንስትራክሽን መሣሪያ አከራይ ዝቅተኛ ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ ያለው ታክስ ከፋይ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሰረት ተፈጻሚ ይደረጋል፡፡

መ) ከአንድ በላይ የኮንስትራክሽን ተሽከርካሪዎች ወይም የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች አከራይ የሆነ ግብር ከፋይ ለየመሣሪያው የተመለከተውን ዓመታዊ ገቢ መጠን ተወስዶ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 በተቀመጠው ሠንጠረዥ መሰረት ተሰልቶ ግብር የሚወሰን ይሆናል፡፡

ሰ) የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ወይም ተሽከርካሪ ከሶስተኛ ወገን ማስረጃ ማግኘት ከተቻለ መረጃው ወይም የገቢዎች ጽህፈት ቤቱ ወቅታዊ የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ኪራይ ጥናት በማነጻጸር የተሻለው ተወስዶ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 በተቀመጠው ሠንጠረዥ መሰረት ተሰልቶ ግብር የሚወሰን ይሆናል፡፡

ረ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ 3 ከተደነገገው ውጭ የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ወይም ተሽከርካሪዎች ግብር ለመወሰን የሶስተኛ ወገን የግብይት መረጃን ወይም የቀን ገቢ ግምት ጥናትን መሰረት በማድረግ ጠቅላላ አመታዊ ገቢ በማግኘት የሚሰላ ይሆናል፡፡

5/ የውጭ ሀገር አሠሪና ሠራተኛ አገናኝነት ሥራ

ሀ) የውጭ አገር አሰሪና ሰራተኛ አገናኝ ሥራ የሚሰሩ ሰዎች በሦስተኛ ወገን መረጃ መሠረት ተደርጎ ግብር የሚወሰንላቸው ይሆናል::

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ጥቅም ላይ የሚውሉ መረጃዎችን ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ፣ ከአየር መንገድ፣ ከኢንሹራንስ፣ ከብሔራዊ ባንክ፣ ከውጭ ጉዳይና ከሌሎች የሚመለከታቸው ተቋማት መረጃውን በማሰባሰብ ዓመታዊ ሽያጫቸው ከ2 ሚሊዮን ብር በታች ከሆነ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 በተቀመጠው ሠንጠረዥ መሰረት ተሰልቶ ግብር የሚወሰን ይሆናል፡፡

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ለ" የተገለጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በአሠሪ ሀገራት ተከፋይ የሚሆነውን የገንዘብ መጠን መረጃ በየግብር

ዘመኑ ተለይቶ ለግብር አወሳሰኑ ጥቅም ላይ የሚውልበት ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኢትዮጵያ የውጭ ስምሪት አገልግሎት ሰጪ ኤጀንሲዎች በየሀገሩ የላኳቸውን ሠራተኞች ብዛት በየግብር ዘመኑ በመለየት በእያንዳንዱ ተጓዥ ዝቅተኛ የአገልግሎት ክፍያ እንደየሀገሩ ከሚመለከተው አካል በሚገኝ መረጃ በመውሰድ ይሰላል፡፡

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ"፣ "ለ" እና "ሐ" የተደነገጉት ቢኖሩም በሀገር ዉስጥ የስራ ስምሪት አገልግሎት የአሰሪና ሰራተኛ አገናኝ ስራ የሚገኝ ገቢ እንደሌሎች የንግድ ዘርፎች በተገኘ የሶስተኛ ወገን የግብይት መረጃ ወይም በተጠናው የቀን ገቢ ግምት መሰረት ግብር የሚወሰን ይሆናል።

10. **የግብር ከፋዮች ደረጃ ሽግግር**

1/ የታክስ አስተዳደር ስርዓቱን ፍትሃዊነት፣ ወቅታዊነት እና ትክክለኝነት ለማረጋገጥ በማናቸውም ሁኔታ የገቢ ጽህፈት ቤቱ ከመደበኛ የቀን ገቢ ግምት ጥናት ወደ ደረጃ "ሀ" መሸጋገር የሚገባቸውን ግብር ከፋዮች በየዓመቱ በማጥናት በገቢያቸው መሠረት የደረጃ ሽግግር ማድረግ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የደረጃ ሽግግሩን ለማድረግ ጥቅም ላይ የሚውሉ ዋነኛ መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ) የንግድ ዘርፍ ለውጥ ሲያደርጉ፣

ለ) ከሦስተኛ ወገን የተገኘው የግብይት መረጃ ከ2,000,000.00 /ከሁለት ሚሊዮን ብር/ እና በላይ

ሲሆን ፣

ሐ) የንግድ እንቅስቃሴ ሲስፋፋ ወይም በዓመቱ ግብይት ሂደቱ ከደረጃ "ለ" ምድብ በላይ መሆኑ

በጥናት ሲረጋገጥ፣

መ) ከተመሣሣይ የንግድ እንቅስቃሴ ካላቸው ግብር ከፋዮች ጋር ሲነጻጸር ለደረጃ ሽግግር የሚያበቃ ግብይት ማድረጋቸውን የገቢ ተቋሙ ሲያምንበት፣ የገቢ ተቋሙ የደረጃ ሽግግር ለማድረግ ሊጠቀምባቸው ይችላል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሰው ቢኖርም ዓመታዊ ግብይታቸው ከብር 2,000,000 ብር/ ሁለት ሚሊዮን/ በታች የሆኑ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች በየዓመቱ ማጥናት ከአስተዳደራዊ፣ ወጪና ከአሠራር መርህ አኳያ አስፈላጊ ባለመሆኑ ጥናት ማካሄድ አያስፈልግም።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አጠቃላይ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች አመታዊ ጠቅላላ ገቢ የሚወሰነው የገቢዎች ቢሮ በየሶስት ዓመቱ በሚያደርገው የገበያ ጥናት ይሆናል።

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የገቢዎች ቢሮ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የሚያወጣውን የዋጋ ግሽበት መረጃ መሰረት በማድረግ በየሦስት ዓመቱ የሚከናወነው የገበያ ጥናት ባልተሰራበት ዓመት በግብር ከፋዮች ጠቅላላ ገቢ ላይ የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ማድረግ አለበት።

ክፍል ሦስት

የደረጃ "ሀ" እና ሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለባቸው ወይም በፈቃደኝነት የሚይዙ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች የግብር አወሳሰን

11. የግብር አወሳሰኑ የሚመለከታቸው የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋዮች

1/ ማንኛውም የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋይ በገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 301/2018 አንቀጽ 84 በተቀመጠው የማሳወቂያ ጊዜ ለደረጃው የሚያስፈልጉ ሰነዶችን አሟልቶ በወቅቱ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም የታክስ ጊዜ ማቅረብ የሚገባውን የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ እንደሆነ

ገቢዎች ቢሮ በማናቸውም ጊዜ የሚያገኘውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ ለታክስ ጊዜው ታክስ ከፋዩ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ በግምት ይወስናል፡
፡

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ በደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋይነት ተመድበው በሕግ በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ ተቀባይነት ያለው የሂሳብ መዝገብ በማቅረብ ገቢያቸውን አስታውቀው በማይከፍሉትና የሂሳብ መዝገባቸው ተቀባይነት ባላገኙት ላይ የግምት ታክስ ስሌት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

12. አመታዊ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ለማግኘት

1/ ለግብሩ አወሳሰን መሠረት የሚሆነው የሽያጭ ገቢ የግብር ከፋዩ የቀን ሽያጭ/ገቢ ሲባዛ የንግድ ዘርፍ የሥራ ቀናት ዓመታዊ የግብር ከፋዩ ገቢ/ ሽያጭ ይሆናል ፡፡(አመታዊ ሽያጭ= የቀን ገቢ* የስራ ቀናት)፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በግብር ከፋዩ ስም የሦስተኛ ወገን መረጃ ከተገኘ መረጃውን ከግብር ከፋዩ የቀን ገቢ ጋር በማነጻጸር የተሻለው የግብር ከፋዩ ዓመታዊ ገቢ/ሽያጭ ሆኖ ይወሰዳል፡፡

13. ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ስለማግኘት

1/ ግብሩ የሚወሰነው በቀን ገቢ ግምት ከሆነ የቀን ገቢ/ሽያጭ ሲባዛ በንግድ ዘርፍ የሥራ ቀናት ተሰልቶ ከሚገኘው ዓመታዊ ሽያጭ ላይ በዘርፉ የትርፍ መቶ መተመኛ ተባዝቶ የሚኝ ውጤት ግብር የሚከፈልበት ገቢ ነው፡፡

2/ ግብሩ የሚወሰነው በሦስተኛ ወገን በተገኘ ግብይት መረጃ ከሆነ አመታዊ ገቢ ሲባዛ በንግድ ዘርፍ የትርፍ መቶ ተሰልቶ የሚገኘው ውጤት ግብር የሚከፈልበት ገቢ ይሆናል፡፡

14. የቤት ኪራይ ገቢ ግብርን በግምት ስለመወሰን

1/በአከራይና በተከራይ መካከል የተፈጸመ የኪራይ ውል ስምምነት የገንዘብ መጠን ትክክለኛነቱ በገቢ ተቋሙ ተቀባይነት ካገኘ በውል ስምምነቱ መሠረት ግብር ይወሰናል፡፡

2/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ግብር ከፋዩ ያቀረበው ማስረጃ ተዓማኒነት ከሌለው እና ከሦስተኛ ወገን መረጃ ከተገኘ ተነጻጽሮ የተሻለው ተወስዶ ግብር ሊወሰን ይችላል ፡፡

3/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት መወሰን ካልተቻለ በክልሉ ታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 3 መሠረት ወቅታዊ ትክክለኛ የኪራይ ዋጋ ጥናት ተወስዶ የግብር ስሌቱ የሚሰራ ይሆናል፡፡

4/ የደረጃ “ሀ” ወይም ሂሳብ መዝገብ እንዲያቀርብ የሚገደዱ የደረጃ “ለ” ወይም በፈቃደኝነት ሂሳብ መዝገብ የሚያቀርብ የደረጃ “ለ” ግብር ከፋይ ግብሩ በግምት በሚሰላበት ጊዜ ከግብር ዓመቱ ጠቅላላ የኪራይ ገቢው 35% እንደ ወጪ ተይዞ 65% ግብር የሚከፈልበት ገቢ ሆኖ በሠንጠረዥ “ለ” መሠረት ይሰላል፡፡

5/በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች በስተቀር በድርጅቶች የኪራይ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የግብር ምጣኔ 30% (ሰላሳ በመቶ) ነው፡፡

6/የደረጃ “ሀ”፣ ሂሳብ መዝገብ እንዲያቀርቡ የሚገደዱ የደረጃ “ለ” ፣ በፈቃደኝነት ሂሳብ መዝገብ የሚያቀርቡ ደረጃ “ለ” ወይም የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ የቤት ኪራይ ገቢ ግብር ከፋይ የሆኑ ግብር ከፋዮች ግብራቸው በግምት የሚወሰን ከሆነ በበጀት የዓመቱ

በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 4 በተመለከተው ምጣኔ መሰረት እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

15. የንግድ ስራ ገቢ ግብር በግምት አወሳሰን

1/የደረጃ "ሀ"፣ ሂሳብ መዝገብ እንዲያቀርብ የሚገደድ የደረጃ "ለ"፣ በፈቃደኝነት ሂሳብ መዝገብ የሚያቀርብ ደረጃ "ለ" ነባር ግብር ከፋይ ዓመታዊ ገቢ በትርፍ መቶ መተመኛ ከተሠላ በኋላ በሚገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ በሠንጠረዥ "ሐ " መሠረት ግብሩ ይወሰናል፡፡

2/ ግብር ከፋዮች ገቢ ያገኙት ከተለያዩ ዘርፎች ከሆነ ከየዘርፉ የተገኘው ዓመታዊ ገቢ በትርፍ መቶ መተመኛው ተባዝቶ የተገኘውን ግብር የሚከፈልበት ገቢ በማዳመር ግብሩ በጣምራ አወሳሰን በሠንጠረዥ ሐ መሠረት ይወሰናል፡፡

3/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አዲስ ወደ ደረጃ "ሀ" ያደጉ ግብር ከፋዮች የግብር ውሳኔው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ግብራቸው የሚወሰን ሲሆን ለደረጃው የተሰጠውን ግዴታ በሚቀጥለው ዓመት እንዲወጡ በደብዳቤ እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል።

4/ በአማራ ክልል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 301/2018 አንቀጽ 19 ንኡስ አንቀጽ 6 መሰረት የጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ እንደ ግለሰብ ግብር ከፋይ አመታዊ ሽያጭን መሰረት አድርጎ የደረጃ ፍረጃ ይሰጣቸዋል::

5/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የግብር አከፋፈላቸውም ደረጃቸውን መሰረት አድርጎ በሂሳብ መዝገብ ወይም በቀን ገቢ ግምት ወይም በሶስተኛ ወገን መረጃ ሁኖ የደረጃ "ሀ" እና ሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለባቸው ወይም በፈቃደኝነት የሚይዙ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች በዘርፉ የትርፍ መቶ መተመኛ እየተሰላ ግብር የሚከፈልበት ገቢ እየተወሰደ በሰንጠረዥ ሐ መሠረት ግብሩ ይወሰናል፡፡

6/በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች በስተቀር በድርጅቶች የንግድ ሥራ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የግብር ምጣኔ 30% (ሰላሳ በመቶ) ነው።

7/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት የሂሳብ መዝገብ ካልያዙ ወይም ያቀረቡት የሂሳብ መዝገብ በማናቸውም ሁኔታ ተቀባይነት ካላገኘ በሶስተኛ ወገን መረጃ ወይም በቀን ገቢ ግምት ጥናት መሰረት ግብሩ የሚወሰን ይሆናል።

8/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 አፈጻጸም የግብር አወሳሰኑም አማካይ የቀን ገቢ ሲባዛ በንግድ ዘርፉ የስራ ቀናት በሚገኘው ገቢ ላይ በዘርፉ የትርፍ መቶ መተመኛ በማስላት ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ ከተደረሰ በኋላ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሠንጠረዥ ሐ መሠረት ይወሰናል።

9/ በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁ ኢንተርፕራይዞችን ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ወይም አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ መሆናቸውን መለየት እንዲቻል ግብር ከፋዮች ማረጋገጫ ደብዳቤ ከሥራና ክህሎት ጽህፈት ቤቶች የማቅረብ ግዴታ አለባቸው።

10/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 መሠረት ጥቃቅን ወይም አነስተኛ ኢንትርፕራይዝ መሆናቸውን ማረጋገጫ ደብዳቤ ከሥራና ክህሎት ጽ/ቤቶች ማቅረብ ካልቻሉ ገቢዎች ቢሮ እንደ አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ቆጥሮ ግብር ሊያስከፍል ይችላል።

11/ የተሸከርካሪና ወፍጮ ንግድ ስራ ያላቸው ዓመታዊ ገቢያቸው 2 ሚሊዮን እና በላይ ሆኖ የሂሳብ መዝገብ ካላቀረቡ ወይም አቅርበው ተቀባይነት ያላገኙ በመደበኛ ቁርጥ ግብር ሠንጠረዥ መሠረት ግብር የሚከፈልበት ገቢ እየተወሰደ ከተደመረ በኋላ ፍሬ ግብሩ በንግድ ግብር ማስከፈያ ሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት እየተሰላ ግብር ይወሰናል።

16. የተጨማሪ እሴት ታክስ አወሳሰንና አሰባሰብ

1/ ቤቱ የተከራየው ከመኖሪያ አገልግሎት ውጭ በሚሆንበት ጊዜ ለኪራይ ገቢ የግምት አወሳሰን ጥቅም ላይ የዋለው የገቢ መጠን እንደአግባብነቱ ለተጨማሪ እሴት ታክስ አወሳሰን መሠረት በመሆን ሊያገለግል ይችላል ::

2/ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይ የሆኑ ግብር ከፋዮች ታክሱን በሕግ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ አስታውቀው መክፈል ይጠበቅባቸዋል::

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በቀን ገቢ ጥናቱ አመታዊ ታክስ የሚከፈልበት ገቢያቸው ከብር 2,000,000.00 (ሁለት ሚሊዮን) እና በላይ ከሆነ ወዲያውኑ ለተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲመዘገቡ መደረግ ይኖርበታል::

4/ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት ግዴታቸውን መወጣት አለባቸው::

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ግዴታቸውን በአግባቡ የማይወጡ የደረጃ "ሀ" እና "ለ" የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ግብር ከፋዮች ታክሱን በትክክልና በወቅቱ ካልከፈሉ ገቢ ጽ/ቤቱ በልዩነት ታክሱን ወስኖ ማሰከፈል ይኖርበታል::

ክፍል አራት
የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋዮች የወል ድንጋጌዎች

17. አስተዳደራዊ ቅጣት

1/ ገቢያቸውን በሂሳብ መዝገብ እንዲያሳውቁ የማይገደዱ ወይም በፈቃደኝነት ሂሳብ መዝገብ የማያቀርቡ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች በቀን ገቢ ግምት ጥናት መሠረት የግብር ውሳኔው ተወስኖ በደረሳቸው በ30 ቀናት ውስጥ ግብር ከፋዩ ግብርና ታክስ መክፈል ይኖርበታል::

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ላይ የተቀመጡት አስተዳደራዊ ቅጣቶች መካከል አዘግይቶ በመክፈል ቅጣት እና ወለድ የሚከፍሉ ይሆናል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም ሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ወይም በፈቃደኝነት ሂሳብ መዝገብ የሚይዝ የደረጃ "ለ" እና ማንኛውም የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች በክልሉ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ላይ የተቀመጡ ግዴታዎችን ባለመወጣት የሚጣሉ አስተዳደራዊ ቅጣቶች እና ወለድ የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው፡

4/ ከዚህ ቀደም የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች የነበሩ እንዲሁም ከአሁን በፊት በግብር መረቡ ያልታቀፉ አዲስ ግብር ከፋዮች፤

ሀ) በጥናቱ ደረጃቸው "ለ" የነበሩ ወደ ደረጃ "ሀ" የተሸጋገሩ፤

ለ) ደረጃቸው ከዚህ ቀደም የማይታወቁ በጥናቱ ደረጃ "ሀ" ሲገቡ

በግብር ከፋዩ የደረጃቸው ለውጥ ምክንያት ከሚጣሉ ማናቸውም አስተዳደራዊ ቅጣቶች የደረጃ ሽግግር ላደረገበት ዓመት ነፃ ይሆናሉ፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ደረጃቸው የተሸጋገረ ግብር ከፋዮች ከሚቀጥለው በጀት ዓመት ጀምሮ ግዴታቸውን ካልተወጡ አስተዳደራዊ ቅጣቱ እንደማንኛውም የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ በክልሉ የገቢ ግብር እና የታክስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

6/ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች ገቢያቸውን በህግ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ገቢያቸውን ካላሳወቁ ወይም የሂሳብ መዝገብ መያዝ ሲገባቸው ካላቀረቡ ወይም የሂሳብ መዝገባቸው በገቢ ጽ/ቤት ተቀባይነት ካላገኘ ወይም ግብሩ አንደገና በልዩነት ከተወሰነ በክልሉ የታክስ አሰተዳደር አዋጅ መሰረት አስተዳደራዊ ቅጣትና ወለድ እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

18. የግብር በዛብኝ ቅሬታ እና ይግባኝ አቀራረብ ስርአት

1/ ግብር ከፋዩ የግብርና ታክስ አወሳሰን ላይ ቅረፊታ ካለው በታክስ አስተዳደር አዋጁ እና ደንቡ መሰረት የግብርና ታክስ ውሳኔው በደረሰው በ21 ቀናት ውስጥ ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ቅሬታውን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል።

2/ የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴው የግብር ከፋዩን ቅሬታ መርምሮ በማሻሻል (በመቀነስ ወይም በማጽናት ወይም በመጨመር) ውሳኔውን ለግብር ከፋዩ የማሳወቅ ኃላፊነት አለበት።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የአቤቱታ አጣሪ ኮሚተው ውሳኔ የደረሰው ግብር ከፋይ የተሻሻለው የግብርና ታክስ ውሳኔው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አከራካሪ የሆነውን ግብር/ታክስ ቅጣትንና ወለዱን ሳይጨመር 50% በቅድሚያ በመክፈል ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በግብር/ታክስ ውሳኔው ላይ ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታ ያላቀረበ ግብር ከፋይ በቀጥታ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ኮሚሽን ይግባኝ መጠየቅ አይችልም፡

19. የተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸዉ ሕጎች

1/ በአማራ ብሔራዊ ክልል ውስጥ ለሚገኙ የደረጃ "ሀ"፣ "ለ" እና "ሐ" ግብር ከፋዮች የግብር አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 15/2015 ዓ.ም በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

2/ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም

20. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በቢሮዉ ጸድቆ፣ በአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ ከተመዘገበ በኋላና በግንዘብ ቢሮዉ የድረ ገጽ አድራሻ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

21. ስለመመሪያው መጽደቅ፣ መመዝገብና በድረ ገጽ መጫን

ይህ መመሪያ

1/ ሀምሌ 23 ቀን 2018 ዓ.ም በግንዘብ ቢሮ ጸድቋል።

2/ ሀምሌ 24 ቀን 2018 ዓ.ም በአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ ተመዝግቧል።

3/ ---------- ቀን 2018 ዓ.ም በግንዘብ ቢሮ ድረ ገጽ ተጭኗል።

ባሕርዳር
ሀምሌ 23/2018 ዓ.ም

አታላይ ጥላሁን ጫኔ
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
የግንዘብ ቢሮ ኃላፊ

የአማራ ክልል ገንዘብ ቢሮ			
የንግድ ዘርፍ የተጣራ ትርፍ መቶ መተመኛ እና አማካኝ የስራ ቀናት ሰንጠረዥ አባሪ 1			
የፍቃድ ኮድ	የንግድ ዘርፍ	የሥራ ቀናት	የተጣራ ትርፍ መቶ መተመኛ በ(%)
ዘርፍ፡- ማኑፋክቸሪንግ			
31129	የእንሰሳት መኖ መፈብረክ	300	10
31115	ወተትና የወተት ተዋፅኦ መፈብረክ	300	10
31121-1	ዳቦና ኬክ መፈብረክ	300	15
31111-1	ልኳንዳ ንግድ /የዕርድ አገልግሎት/ ስጋ በኪሎ መሸጥ፣ ክትፎ ብቻ መሸጥ፣ ሽንኩርትና ስጋ መፍጨት አገልግሎት	210	13
38115	የትራንስፖርት ተሽከርካሪና ተጎታች መስራት	300	15
31115-1	ጥሬ ወተት ችርቻሮ	300	10
31111	ሥጋና የስጋ ዉጤቶች ማቀነባበርና መጠበቅ	300	16
31112	ለምግብነት የሚዉሉ የባህር እንስሳትና ምርታቸውን ማቀነባበርና መጠበቅ	300	16
31113	አትክልትና ፍራፍሬ ማቀነባበርና መጠበቅ	300	16
31114	የምግብ ዘይት መፈብረክ	300	10
31116	የእህል ምርት ውጤቶችን መፈብረክ	300	16
31117	ስታርችና የስታርች ዉጤቶችን እና ማጣፈጫ መፈብረክ	300	16
31118	ፈጣን ምግቦችን መፈብረክ	300	16
31121	ዳቦና ኬክ መፈብረክ	300	15
31122	ስኳር መፈብረክ	300	11
31123	ጣፋጭ ምግቦችን መፈብረክ (ብስኩት፣ ቸኮላት፣ ካካዎ፣ ካራሜሊንና ማስቲካን ይጨምራል)	300	10
31124	ጨው መፈብረክ	300	13
31125	ፓስታ፣ ማካሮኒ እና ተመሳሳይ ምርቶችን መፈብረክ	300	14
31126	ማርና የማር ውጤቶችን መፈብረክ	300	13
31127	ቡናና የሻይ ቅጠል መፈብረክ	300	10
31128	የመኖ ጥሬ ዕቃ መፈብረክ	300	10
32111	የመጠጥ ውኃ መፈብረክ	300	25
32112	ከአልኮል ነፃ የሆኑ መጠጦችን መፈብረክ (የመጠጥ ውኃን ሳይጨምር)	300	25
32113	የአልኮል መጠጦችን መፈብረክ	300	25
32211	የትምባሆ ምርቶች መፈብረክ	300	26
33111	መፍተል፣ መሸመንና የጨርቃ ጨርቅ ምርቶችን ማጠናቀቅና መፈብረክ (አልባሳትን ሳይጨምር)	300	10
33112	አልበሳትን መፈብረክ (የፀጉር አልባሳትን ጨምሮ)	300	10
33113	ምንጣፍ እና ስጋጃ ማምረት	300	10
33114	ከጭረትና ከጭረት ውጤቶች የተሰሩ መያዣዎችና	300	16

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በአማራ ክልላዊ መንግስት
ገንዘብ ቢሮ
Bureau of Finance
ገንዘብ ቢሮ

	ማሽኒያዎች መፈብረክ		
33115	የሹራብና የኪሮሽ ፋብሪክስና አርቲክልስ መፈብረክ	300	10
33211	ቆዳና ሌጦ ማለስለስና ማጠናቀቅ	300	21
33212	ሰዉ ሰራሽ የሆኑ የቆዳ ምትክ ምርቶች መፈብረክ	300	21
33213	የተዘጋጁ የቆዳና የቆዳ ምትክ አልባሳትና ውጤቶችን መፈብረክ	300	21
33214	ጫማ መፈብረክ	300	18
34111	እንጨትና የእንጨት ውጤቶችን መፈብረክ	300	16
34211	ወረቀትና የወረቀት ውጤቶችን መፈብረክ	300	22
34212	ፐልፕ፣ ወረቀትና የወረቀት ቦርድ መፈብረክ	300	22
34311	ህትመትና ተያያዥ ሥራዎች	300	22
34411	የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መፈብረክ	300	22
35111	የኮክ አሸን ምርቶች መፈብረክ	300	16
35112	የተጣራ የነዳጅ ውጤቶች ማምረት	300	26
35211	መሰረታዊ ኬሚካሎችን መፈብረክ	300	16
35212	ማዳበሪያ እና የናይትሮጂን ውህዶች መፈብረክ	300	16
35213	መሰረታዊ (የመጀመሪያ ደረጃ) ፕላስቲኮችንና ሲንቴቲክ (ሰዉ ሰራሽ) ጎማ መፈብረክ	300	16
35214	ጎማና የፕላስቲክ ውጤቶች ማምረት	300	14
35215	ባትሪዎች ማምረት	300	13
35216	ጸረ ተባይና የግብርና ኬሚካሎችን መፈብረክ	300	21
35217	ቀለም፣ ቫርኒሽ እና ተመሳሳይ ምርቶች እና ማጣበቂያ መፈብረክ	300	16
35311	ለሰዉ አገልግሎት የሚዉሉ የህክምና የመድኃኒትና ኬሚካሎች መፈብረክ	300	21
36911	የመለኪያና የመፈተሻ መሣሪያዎች መፈብረክ	300	16
35312	ለእንሰሳት አገልግሎት የሚዉሉ የህክምና የመድኃኒትና ኬሚካሎች መፈብረክ	300	21
35313	ሌሎች ለመድኃኒት ግብዓትነት የሚዉለ መሰረታዊ የመድኃኒት ዉጤቶችን ማምረት	300	21
35411	የንፅህናና የኮስሞቲክስ እቃዎች እና ግብአቶች መፈብረክ	300	17
36111	ብረት፣ የአረብ ብረት እና የብረት ማዕድናት ውጤቶችን መፈብረክ	300	15
36112	ብረታ ብረት መጠቅለል፣ ማተም ፣ የብረት ዱቄትና የመሳሰሉትን ጨምሮ መፈብረክ	300	15
36211	መስታወት እና የመስታወት ውጤቶች መፈብረክ	300	10
36212	ሲሚንቶ፣ ኖራ እና ለመለሰኛ የሚያገለግለ ምርቶችን መፈብረክ	300	18
36214	ለስትራክቸር ስራ የሚውል የሸክላና የሴራሚክ ውጤቶችን መፈብረክ	300	10
36215	የድንጋይ ውጤቶችን መፈብረክ	300	18
36216	ብረታ ብረት ያልሆኑ የማዕድናት ውጤቶችን መፈብረክ	300	16

36311	ማዕድናትን ማንጠር	300	16
36312	ማዕድናት ማቅለጥ/ማድለብ	300	16
36313	ብረት እና ማግኔታዊ ያልሆኑ ብረታ ብረቶች ማቅለጥ /ማድለብ	300	16
36314	ማግኔታዊ ያልሆኑ (አልሙኒየም፣ ዚንክ፣ ሉዴ፣ ታንታሆም፣ ኒኬል፣ ነሐስ ከመሳሰሉት) የብረታ ብረት ውጤቶችን መፈብረክ	300	16
36411	ለስትራክቸር የሚያገለግል የብረታብረት ውጤቶች መፈብረክ	300	16
36511	ለሁለገብ ሥራ የሚያገለግል መሣሪያዎች መፈብረክ	300	16
36512	ለልዩ አገልግሎት የሚውሉ መሣሪያዎችን መፈብረክ	300	16
36611	የጦር መሣሪያዎች እና ጥይቶች መፈብረክ	300	16
36711	የኤሌክትሪክ መሣሪያዎችና መገልገያዎች መፈብረክ	300	16
36811	የመገናኛ መሣሪያዎች፣ መለዋወጫዎች እና መገልገያዎች መፈብረክ	300	16
37111	የጨረራ አመንጪ መሳሪያዎችና ቁሶችን መፈብረክ	300	16
37211	የፎቶ ግራፍና የዕይታ መሣሪያዎችን መፈብረክ	300	16
37311	ለህክምና መገልገያነት የሚውለ ውጤቶችና መሣሪያዎችን መፈብረክ	300	16
38111	የሞተር ተሽከርካሪዎች መፈብረክ	300	15
38112	የተሽከርካሪዎች አካላት፣ መለዋወጫዎችና ጎማዎች መፈብረክ	300	13
38113	የሞተር ብስክሌቶችን መፈብረክ	300	15
38114	ብስክሌቶችና ጋሪዎችን መፈብረክ	300	15
38211	መርከቦችንና ጀልባዎችን መገንባት	300	16
38212	በባቡር እና በትራም መንገድ የሚሄዱ ሎኮሞቲቮችን እንዲሁም ዘዋሪ እግር ያላቸውን ተሽከርካሪዎችን መፈብረክ	300	16
38213	የአውሮፕላንና የጠፈር መንኩራኩሮችን መፈብረክ	300	16
39111	የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ማምረት	300	16
39112	የስፕሪንግ ስፖንጅና ፎም ውጤቶችን መፈብረክ	300	10
39113	ኮምፒውተር፣ የኮምፒውተር መሣሪያዎችና መለዋወጫዎችን መፈብረክ	300	16
39121	የመዝናኛ ዕቃዎች መፈብረክ	300	16
39131	የእደጥበብ፣ የገፀበረከት ዕቃዎች እና አርቲፊሻል ጌጣጌጥ መፈብረክ	300	14
39141	ሶፍትዌር መፈብረክ (ዲዛይን ማድረግ፣ ማበልጸግና ትግበራን ያካትታል)	300	16
39142	የዕህፈት መሳሪያዎች መፈብረክ (ከወረቀትና የወረቀት ውጤቶች በስተቀር)	300	16
39143	ቁልፍ፣ መያዣ፣ ተንሸራታች ማያያዣ ወዘተ መፈብረክ	300	16
39144	የቁጥር ሰሌዳ፣ ምልክቶች እና የማስታወቂያ ሰሌዳ	300	16

	(በኤሌክትሪክ የማይሰሩ) መፈብረክ		
39145	ውድቅዳቂዎችና ስክራፖችን ጥቅም ወዳላቸው ምርቶች መለወጥ/መፈብረክ	300	16
39146	መጥረጊያና መወልወያ መፈብረክ	300	16
36213	ከኮንክሪት፣ ከሲሚንቶና ከመለሰኛ የሚሰሩ ውጤቶችን መፈብረክ	260	25
ዘርፍ:- ኮንስትራክሽን			
51212-1	መስታወት ስራ እና ንግድ	300	10
